

ፍጹም መንገሻ(ኖርዌይ)

# መስዋእትነት አይቀሬ ነው

# የትኛው ይሻላል??

በሃገራችን እንደ አለመታደል ሆኖ ህዝብን የሚወክል በህዝብ የተመረጠ መንግስት ሳይኖረን ይህንን እድል ለመፍጠር እድሉ የነበራቸውም ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች ከህዝብ ፍላጎት እና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግል ጥቅማቸውን እና የባእዳኖችን ፍላጎት በማስቀደም ያገኙትን የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም የህዝብን ስልጣን እየነጠቁ ለህዝብ እና ለሃገር የቆሙትን እየገፉ እና እየገደሉ በጉልበት መንግስት ነን እያሉ ህዝብን  በማገልገል ስራ ሳይሆን የየራሳቸውን ጥቅም በማስጠበቅ እና በስልጣን ለመቆየት እንደተጠመዱ የህዝብን ሃብት ለግል ጥቅማቸው እያዋሉ  ህዝብን እንዳሻቸው እየጨቆኑ እያንገላቱ ቆመንለታል የሚሉትን ህዝብ እየጨፈጨፉ ሃገርን እየጎዱ ለትውልድ የሚተርፍ ታሪክ የማይረሳው የጥፋት አሻራ ጥለው ያለፉ እና እያለፉ ያሉ የተለያዩ ስርዓቶችን እያስተናገደች አለች፡፡ከነዚህም ውስጥ አንዱ ከፋሺስት ደርግ ስልጣኑን የተረከበው አሁን በስልጣን ያለው ዘረኛው የወያኔ ስርአት ነው፡፡ የፋሺስት ደርግ ስርዓት ለሃገር እና ለህዝብ የቆሙትን በመጨፍጨፍ እንደሚታወቀው ሁሉ አሁን በአገዛዝ ያለው ስርዓትም የራሱ የሆነ ጸረ ህዝብ እና ጸረ ሃገር የሆኑ መለያዎች አሉት፡፡

የወያኔ ስርአት ከባለፉት ጨቋኝ ስርዓቶች ለየት የሚያደርጉት በርካታ እኩይ ባህሪያቶች እዳሉት ግልጽ ነው፡፡ ስርአቱ የሚታወቅበት መቼም ሊለወጥ እና ሊሻሻል የማይችል አያሌ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ህዝብ አጀንዳዎች እንዳሉ ሆነው በተጨማሪ ካሉት ባህሪያቶቹ አንዱ በተሳሳተ  እና በአለቆቹ በባእዳን የተነገረውን ለባእዳኖች ባለመዘዙ የሚታወቀን የኢትዮጵያን ህዝብ ለመበቀል እና ኢትዮጵያን ለመበታተን እና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተዘጋጀውን የተሳሳተ ታሪክ ይዞ በተለይም ለስርዓቱ አልገዛም ባለው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ቂም እየያዘ ለመበቀልም ከፍተኛ በጀት እና  የሰው ሃይል መድቦ ለጥፋት መነሳቱ ባጠቃላይ ቂመኛነቱ እንደሆነ የቂሙ ጽዋ የደረሰው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ባህሪው ነው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ወያኔ በበሬ ወለደ ታሪክ በአማራው ህዝብ ባጋምቤላ እና  በተላያዩ በዘር ያስቀመጣቸው ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ባላቸው ላይ የሚያደርሰው ቂም በቀል የዘር ማጥፋት ዘመቻ መከራና  እንግልት፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊትን በትኖ ወደ ልመና እስከ ማውጣት የደረሰ ብቀላ፤በራሱ አባላት የግልበጣ ሴራ አካሂዳችኋል በማለት ያጠፋቸው በህይወትም ያሉትን የሚያደርስባቸው የብቀላ እንግልት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም የአዲስ አበባ ህዝብ በ1997 ምርጫ ወያኔን ባለመምረጡ እየደረሰበት ያለው መከራ እና ስቃይ የወያኔን ቂመኛነት በይበልጥ የምናረጋግጥባቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡አሁንም ቂመኛው ስርዓት በስልጣን እስካለ ድረስ ህዝብም አልገዛም ማለቱን መቀጠሉ እንደማይቀረው ሁሉ የስርአቱም ባህሪ የሆኑ የብቀላ

ሂደቶች ቀጣይ ይሆናሉ ማለትነው። ታዲያ የቱ ይሻላል ህዝብ ስርዓቱን በመቃወሙ ለብቀላው የሚከፍለው መስዋእትነት? ወይስ ለአንዴና ለመጨረሻ መስዋእትነት ከፍሎ ይህን ዘረኛ ስርዓት ማስወገድ ??

እንደሚታወቀው በመሳሪያ ጋጋታ እና በህግ ብዛት ሃሳቡን እና ተቃውሞውን እንዳይገልጽ የተከለከለው የኢትዮጵያ ህዝብ የተፈጠሩትን አጋጣሚዎች በመጠቀም ህዝባችን ለስርዓቱ ያለውን እምቢተኝነት እና የወያኔን ማንነት ባገኘው አጋጣሚ እየገለጸ ይገኛል ከዛም አልፎ የወያኔን የምርጫ ድራማ ላይ ባለመሳተፍ እና ባለመምረጥ ለስርዓቱ ያለውን አቅዋም አሳይቷል። በመሆኑም በቂመኛነቱ ለሚታወቀው ይኸው የወያኔ ቡድን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በስልጣን መቆየቱ የቂሙን ደረጃ የት ያደርሰዋል? ስልጣኑንስ የሚጠቀመው እውነት ሃገር እና ህዝብን ለመጥቀም ነው? ወይስ የቆመለትን ኢትዮጵያን የማጥፋት ዘመቻውን እና ቂሙን ለመበቀል ጊዜ ስለሚያሻው?የሆነው ሆኖ ህዝብም ወያኔን ሊቀበል የሚችልበት የወል አላማ ባለማግኘቱ ዛሬም ሆነ ነገ ሊመርጠው አልቻለም አይችልምም።አጥፊ እና ጠፊ አብረው መኖር እንደማይችሉ ሁሉ መቼም ቢሆን ህዝብ ከወያኔ ጎን ሊቆም አይችልም። ህዝብ ወያኔን ባለመምረጡም ሆነ ከወያኔ ጎን እስካልቆመ ድረስ ደግሞ ወያኔም ለዚህ ምላሽ መስጠቱ አይቀርም ማለትም ህዝባችን የተለመደ የወያኔን ቂም በቀል እርምጃ በእጥፍ መቀበሉ አይቀሬ ነው።ወያኔ በስልጣን እስካለ ድረስ ህዝብ ወያኔን ባለመምረጡ የሚደርስበት የዘር ማጥፋት ዘመቻ፤እስራት፤ ድብደባ፤ አፈና፤ የሴቶች መደፈር፤ ብሄራዊ ውርደት፤ በኑሮ ውድነት መሰቃየት፤ ከኖረበት መፈናቀሉ ሌላም ሌላም በከፋ ሁኔታ ይቀጥላል።ይህ ደግሞ ህዝብ ለስርአቱ ያለውን ጥላቻ በመግለጹ ወይም ባለመቀበሉ ምክንያት በቁሙ የሚከፍለው አንደኛው ዓይነት መስዋእትነት ነው።ሌላኛው መስዋእትነት ደግሞ ይህ ስርአት በስልጣን በቆየ ቁጥር እየመጣ ያለውን እና የሚመጣውን ጭቆና፤ መከራ የጀነሬሽን ጥፋት ባጠቃላይ የሃገር ጥፋት ለመከላከል ወይም ባለበት ለማቆም ከዛም አልፎ ህዝባችን ለዘመናት የተጠማውን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በሃገራችን ለመገንባት፤ በህዝብ የተመረጠ ህዝባዊ መንግስት ለማቋቋም፤ የሃገር ሉአላዊነትን ለማስጠበቅ፤ ብሄራዊ ውርደትን ለማስቆም አማራጩ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ የሆነውን ይህን ስርዓት እስከመጨረሻው ለማስወገድ የሚከፈል መስዋእትነት ነው።

በስርአቱ ቅኝ አገዛዝ ስር የወደቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ወደም ጠላ ይህ ስርዓት እስከቀጠለ ድረስ ከእነዚህ አንዱን መስዋእትነት መክፈሉ አይቀርም የትኛው ይሻላል የሚለውን መምረጥ የህዝብ ቢሆንም ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ታሪክ አንጻር ሲታይ መቼም ቢሆን ዝም በማለት ሃገር ስትሸጥ እያየ ይህን ሁሉ መከራና ስቃይ እያየ መሞትን ይመርጣል ተብሎ አይገመትም በሌላላ አነጋገር ይህኛውን አይነት መስዋእትነት የመርጣል ተብሎ አይጠበቅም በሌላ በኩል ህዝባችን ሁለተኛውን ዓይነት መስዋእትነት ለመክፈል ቢዘጋጅም ለተግባሩ ከአገዛዙ እና ከአጋሮቹ ትግልን የማደናቀፍ ሴራ ጀምሮ ሌሎችም ደንቃራ የሆኑበት በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ የታወቀ ነው። አሁን ላይ ግን እንቅፋቶች አሉ ብሎ ፊትን ከትግል ከማዞር ይልቅ እየተካሄደ ያለውን የጥፋት ስፋት በመመርመር እንቅፋቶችን እየጠረግን ትግላችንን ማጠናከር ብቻ ሳይሆን ይህን ስርዓት ለማስወገድ ለሚጠይቀው መስዋእትነት መዘጋጀት ህዝባዊዉን ሃገር አድኑን ትግሉን መቀላቀል የሁሉ ግዴታ ነው። ህዝባችን በዘሩ በፖለቲካ አስተሳሰቡ በሌሎችም እየተመረጠ መስዋእት መሆኑ ላይቀር ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በማጥፋት ዘመቻ ውስጥ ሰለባ መሆኑ እስካልቀረ ድረስ እራሱን መስዋእት አድርጎ ብሄራዊ ክብራችንን ለማስመለስ፤ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሃገራችንን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ፤ እውነተኛና ያልተገደበ ዲሞክራሲ በሃገራችን ለመገንባት፤ ለህዝብ እና ለሃገር ተቆርቋሪ የሆነ በህዝብ የተመረጠ መንግስት በሃገራችን ለመመስረት በሚደረገው ትግል ላይ የሚጠየቀውን መስዋእትነት በመክፈል ከባለፉት ከድጡ ወደማጡ የስርአት ለውጦች በመማር የሚመጣው ለውጥ ለተወሰነው ህብረተሰባችን ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ይጠቅም ዘንድ ዛሬም የባለፉት አይነት ጨቋኝ ስርዓቶች

ተመልሰው እንዳይመጡ የተስተዋለ አደረጃጀት በመደራጀት ጊዜው የሚጠይቀውን መስዋእትነት በመክፈል አንድ በመሆን እና ህዝባዊ አመጽን በማፋፋም ዘረኛውን ስርዓት በማስወገድ ሃገራችን ኢትዮጵያን እንታደጋት። በየስርአቱ የተጨቆነውን የተገፋውን ህዝባችንን አለኝታ እንሁንለት።

## ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ለዘላለም ይኖራሉ!!!